# ከግሪድ ውጪ የታሪፍ ማመልከቻና መረጃ ማቅረቢያ

# አሰራር

# OFF GRID TARIFF APPLICATION AND INFORMATION SUBMISSION PROCEDURE

ሐምሌ 2013

July 2021

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

**ዓላማ**

ይህ መመሪያ ከግሪድ ዉጭ ላሉ የንግድ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አልሚዎች ተፈጻሚ ይሆናል

## 1. የመረጃ አቅርቦት

የኢትዮጵ ኢነርጂ ባለስልጣን የቁጥፅር ማእቀፉ ባጠቃላይ በተለይም ደግሞ የታሪፍ ትመና ሂደት ተዓማኒነት እና ተቀባይነት ያለው ግልፅ የቁጥጥር ስርዓት የመፍጠር ኃላፊነት አለበት፡፡ ሥለዚህም ባለስልጣኑ ባለፉት አመታትና ወራት ውስጥ ከታሪፈ አተማመንና ቁጥጥር አሰራር ጋር በተያያዘ በርካታ መመሪያዎችን እንደ፤ የአነሰተተኛ ግሪድ መመሪያ፤አንድ ወጥ ሂሳብ አያያዝ መመሪያ፤ የአገልግሎት ጥራት ደረጃ መመሪያዎችን ጥልቅ የሆኑ የምክክርና የማስወሰን ሂደቶችን በማለፍ ጸድቀው አሁን በትግበራላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ አሰራር የእነዚህን መመሪያዎች ተፈጻሚነት ለማመቻቸት ተብሎ የወጣ ነው፡፡

ስለሆነም ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ፣ ሚስጥራዊ ተደርጎ መወሰድ አለበት ብለዉ የሚያስቡትን ማንኛዉንም መረጃ ማቅረብ የባለፈቃዶቹ ኃላፊነት ነው፡፡ ይህ ቢሆንም የመረጃዉን ሚስጥራዊነት የመስጠት ዉሳኔ የባለስልጣኑ ብቻ ይሆናል፡፡

በዚህ ሰነድ ዉስጥ የቀረቡት መስፈርቶች በአብዛኛዉ ለታሪፍ ትንተና የሚያስፈልጉ ቁልፍ መረጃዎችን ለመያዝ የተቀረጹ መሆናቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው

**Scope**

This guideline sis applicable for developers of commercial electricity services in an off grid area

## 1. Information Submission

Ethiopian Energy Authority has a responsibility to create a *transparent regulatory system* to enhance the credibility and acceptance of the regulatory framework in general, and in the tariff-setting process in particular. Towards this end the Authority, over the years and months, has developed a number of directives relevant to rate setting and these Directives includes: Mini Grid Directive, Uniform system of Account, Quality of service standards etc. after rigours consultation and approval process are now under implementation. This Procedure is therefore issued to facilitate the effective enforcement of these directives.

Among others, while submitting data and information to the Authority. It is therefore the responsibility of the licensees to bring EEA's attention to any information which they feel should be treated as confidential. This notwithstanding, the final decision to grant such confidentiality shall be ***determined solely by Authority.***

It is also important to note that while the requirements presented in this document are designed to capture most of the key information required for tariff analysis, EEA may still request

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

ባለስልጣኑ በቀረቡ በማናቸውም ጉዳዮችላይ ተጨማሪ መረጃ ወይንም ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## 2. መረጃ የማስረከቢያ መስፈርቶች

ለታሪፍ ማመልከቻ ባለፈቃዶች መከተል የሚገባቸዉ ዋና ዋና ነገሮች የሚከተሉት ናቸዉ

ሀ) አጠቃላይ መስፈርቶች እና የታሪፍ ማመልከቻ መሰረታዊ ምክንያት

ለ. የፋይናንስ መረጃ

- ➢ አጠቃላይ የፋይናንስ መረጃ
- ➢ ለታሪፍ ማመልከቻ ጋር ተያያዥነት ያለዉ የፋይናንስ መረጃ

ሐ. የቴክኒካልና የስራ መረጃ

### 2.1 አጠቃላይ መስፈርቶችና መሰረታዊ ምክንያት

- ባለፍቃዶች ለታሪፍ ማመልከቻ ማጠቃለያ እና መሰረታዊ ምክንያት ማቅረብ አለባቸዉ
- ባለፈቃዶች በተለያዩ የማመንጨት፣ የማከፋፈልና የሽያጭ የኤሌክትሪክሲቲ ኢንዱስትሪ ክፍሎች የሚገኙ ወጪዎችን፤ በማመነጨት፤ በማከፋፈልና ሽያጭ ለይተው ማቅረብ አለባቸው፡፡

further information and clarification on any of the items from the licensees, if necessary.

## 2. Submission Requirements

The key elements of the tariff application to be submitted by the licensees are as follows:

i. General requirements and the rationale for tariff application;

ii. Financial Information:

- ➢ General financial information;
- ➢ Financial information relevant to the tariff application;

iii. Technical and operational information;

### 2.1 General Requirements and Rationale

- Licensees must provide a summary and rationale for the tariff application;
- The licensees must disaggregate costs into various segments of the electricity industry namely: Generation, Distribution & Sale;

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

- ባለፈቃዶች ሁሉንም የኢኮኖሚክ፣ የቴክኒክና የፋይናንስ ግምቶችን ማስቀመጥ አለባቸዉ፣

- ባለፈቃዶች ስለሁሉም መረጃዎችና ታሳቢዎች ዝርዝር ማብራሪያዎችን ማቅረብ አለባቸዉ፣
- ባለፈቃዶች እንደአግባቡ ወጪንና ገቢን ቁጥጥር ከሚደረግባቸውና ቁጥጥር ከማይደረግባቸው አንጻር እንዴት ለይተው እንደሚያቀርቡ መነሻ ማቅረብ አለባቸው፡፡
- ሁሉም ደጋፊ መረጃዎች በMSExcel ፎርማት መዘጋጀትና በኤሌክትሮኒክስ ስርዓት መግባት አለባቸዉ፣
- ሁሉም ደጋፊ ሰነዶች እና መረጃዎች በወረቀት ቅጂና በኤሌክትሮኒክስ ስርዓት መቅረብ አለባቸዉ፣
- ዋናዉ የታሪፍ ማመልከቻ በወረቀት ቅጂና በኤሌክትሮኒክስ ስርዓት እንዲሁም በፒዲኤፍ ኤክሴልና ወርድ ፎርማት እንዳግባቡ መግባት አለባቸዉ

## 2.2 የፋይናንስ መረጃ

የታሪፍ ማመልከቻውን በሚገባበት ጊዜ ወደኋላ የሁለት ዓመት ( እንደአግባቡ) እና ወደፊት የአራት ዓመት የትንበያ ጊዜ ዝርዝር የፋይናንስ መረጃ ማሳየት አለበት፡፡

- Licensees must state all assumptions made namely: Economic, Financial and Technical;

- Licensees must provide detailed explanation on all data and assumptions;

- Licensees must provide basis for splitting costs and revenue between regulated and non-regulated business, if applicable;

- All supporting data must be prepared and submitted electronically in MS Excel format;

- All supporting documentation and data must be provided both in hard and as electronic copies;

- The official tariff application must be submitted as a hard copy and also as an electronic copy in PDF Excel and Word formats as appropriate.

## 2.2 Financial Information

- In submitting the tariff application, the line items for financial information must show two years of HISTORICAL FINANCIAL INFORMATION (where

Off grid tariff application and information submission FINAL Procedure July 2021

የፋይናንስ መረጃው የሚከተሉትን መሸፈን አለበት:-

- ከዚህ በፊት የነበሩት ሁለት የፋይናንስ ዓመታት ኦዲት የተደረገ ሂሳብ (እንደአግባቡ)፤
- በታሪፍ ማመልከቻዉ ዓመት የተሻለ ግምት መሰረት
- የአራት ዓመት ትንበያዎች
- የረዥም ጊዜ የፋይናንስ ምንጮች በአነስተኛ ወለድ ምጣኔ ሊገኝ የሚችል ብድርና ስጦታ።

relevant) and a FOUR-YEAR FORECAST period. The financial information has to cover the following:

- The two previous financial years of audited figures(if applicable);
- The year of tariff application based on 'best' estimates;
- Four-year forecasts;
- Sources of long-term finance, including concessionary loans and grants;

## 3. መመሪያዎች

የገቢ መጠንን ለመወሰን የሚያስችሉ ቁልፍ የወጪ አይነቶችን በተመለከተ በባለፈቃዱ የሚቀርቡ መረጃዎች መመሪያ፤

### 3.1 ቁጥጥር የሚደረግበት ንብረት መነሻ (Regulatory Asset Base)

ቁጥጥር የሚደረግበት ንብረት መነሻ (RAB) ላይ ያለው መረጃ የሚከተሉትን ይሸፍናል፤

- የንብረት ዋጋ በኤሌክትሪክ ዘርፍ ዋና ክፍሎች ማለትም፤ የማመንጨት፣ የማከፋፈልና ሽያጭ መሰረት መለየት አለበት፣
- የባለፈቃዱ የኢንቨስትመንት ምጣ

## 3. Guidelines

Guidelines for minimum information to be submitted by the licensees in respect of the key cost components to be used for determination of the revenue requirements:

### 3.1 Regulatory Asset Base

The information on Regulatory Asset Base (RAB) must cover the following:

- Asset values of licensee's own investment must be separated from assets funded from grants, concessionary loans, government investment and customer contributions;
- Asset values of licensee's own

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

ኔበስጦታ በከተገኘ የተገዛ ንብረትን፣ የአነስተኛ ወለድ ብድር፣ ከመንግስት ኢንቨስትመንትና ከደንበኞች መዋጮ ከተገዙ ንብረቶች መለየት አለባቸዉ፣

- ለታሪፍ ማመልከቻ ሲባል ንብረቶች በጥቅም ላይ ሊዉሉ የሚችሉበት የአገልግሎት ዘመን ባለስልጣኑ ባወጣው የአንድ ወየጥ ሂሳብ አያያዝ (Uniform System of Accounts) መመሪያ መሰረት መሆን አለበት፡፡

## 3.2 የካፒታልን ማሳደግና እና በግንባታላይ ያሉ የካፒታል ስራዎች Capital Works-In-Progress (CWIP)

ባለፈቃዱ የካፒታል ማደግ እና የካፒታል ስራዎችን በተመለከተ ከታሪፍ ማመልከቻው ጋር የሚከተሉትን መረጃዎች ያቀርባል፤

- የተጠየቀው ታሪፍ በስራላይ ለሚቆይበት ጊዜ የካፒታል ውጪ ማጠቃለያ፡፡ መረጃው ቢያንስ የሚከተሉትን መያዝ አለበት
  - ➢ የአሁኑ የካፒታል ወጪ፤
  - ➢ በግንባታላይ ያሉ የካፒታል ስራዎች (CWIP)፤
  - ➢ በሥራ ላይ ያሉ ንብረቶች (ተጨማሪ ንብረቶች)፣
  - ➢ የንብረት ማስወገድ ወይም ከስራውጪማድረግ፣

investment must be separated from assets funded from grants, concessionary loans, government investment and customer contributions;

- The estimates of assets useful lives used in the tariff application must be in accordance with the Uniform System of Accounts;

## 3.2 Capital Additions and Capital Works-In-Progress

The licensee is required to provide the following information on capital additions and capital work-in-progress, as part of the tariff application:

- A summary of capital expenditures over the tariff period. The information must at least contain the following:
  - ➢ Actual capital expenditure;
  - ➢ Capital Works-In-Progress (CWIP);
  - ➢ Assets which has entered into operation (i.e. Asset Additions);
  - ➢ Asset disposals or assets abandoned;

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

- ባለፈቃዱ ፣የካፒታል ስራዎች (CWIP) በተመለከተ ዝርዝር ማብራሪያና የንብረቶቹን ዋጋ እና መቼ ወደ ሥራ እንደሚገቡ፣ እንዲህ ዓይነቶቹ ንብረቶች መቼ የቁጥጥር የሚደረግባቸው የንብረት መሰረት እንደሚካተቱ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፤
- ባለፈቃዱ የካቲታል እድገት የግዜ ሰሌዳን፤ስራው የሚጀመርበት፤ስራው የሚጠናቀቅበትንና አገልግሎት መስጠት ባለስልጣኑ እንዲያዉቀዉ ለማስቻል ዝርዝር ማብራሪያ ያቀርባል።
- ባለፈቃዱ በተጨማሪም ለእያንዳንዱ የኢንዱስትሪው ክፍል የታቀደን የአራት ዓመት የካፒታል ወጪ ትንበያ ፕሮግራም ማቅረብ አለበት፤

### 3.3 ንብረትን ማስወገድ

የንብረት አወጋገድን እና ብልሽትን በተመለከተ ቁጥጥር የሚደረግባቸዉ አገልግሎት ሰጪዎች የሚከተሉትን መረጃዎች ማቅረብ አለባቸዉ፤

- የተወገዱና ወይም የተበላሹ/ የተነቀሉ ንብረቶች ዝርዝር ከነምክንያታቸው በማብራሪያ ተደግፎ መቅረብ አለበት፤
- በንብረቱ አወጋገድ ሂደት ወቅት የተገኘው ገቢ ወይም ኪሳራ፤

- Licensee has to provide detailed explanation and asset values of CWIP and show when they will enter into operation, to enable EEA know when such assets would be added to the RAB;
- The regulated utility companies has to provide a schedule of the capital additions showing expected commencement, completion and commissioning dates;
- Licensees must also provide a 4-year forecast of planned capital expenditure programme for each segment of the industry;

### 3.3 Asset Disposal

Regarding asset disposals and impairment, the regulated utilities has to provide the following information:

- List of asset disposed and/or decommissioned. This has to be supported by explanation or reasons for such disposal and decommissioning;
- Revenue generated or loss incurred during the process of the assets disposal;

Off grid tariff application and information submission FINAL Procedure July 2021

- ማንኛውም ኪሳራ/ትርፍ በአንድ ወጥ ወጥ የሒሳብ መመሪያ መሰረት መያዝ አለበት። ማንኛዉም ገቢ/ኪሳራ በገቢ ሒሳብ መግለጫ ክስተቱ በተፈጸመበት ግዜ አንጻር መያዝ አለበት።

## 3.4 የአገልግሎት ተቀናሽ

ቁጥጥር የሚደረግባቸዉ ባለቃዶች የሚከተሉትን የአገልግሎት ተቀናሽ መረጃዎች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

- በታሪፍ ማመልከቻው ላይበወቅቱ ያለዉን የአገልግሎት ተቀናሽ መጠን መጥቀስ፤
- ለእያንዳንዱ የኤሌትሪክ ዘርፍ የንብረት ክፍል የ(Regulatory Asset Base (RAB)) የተጠራቀመ የአገልግሎት ተቀናሽ፤ የዋጋ ቅነሳ
- አሁን ያለው የቅነሳ ዘዴ በሚኒ ግሪድ መመሪያ መሰረት መወሰን አለበት

## 3.5 የስራ ማስኬጃ ካፒታል

በተጨማሪም ባለፈቃዱ ስራውን በቀጣይነት ለማስኬድ የሚያስፈልገውን የስራ ማስኬጃ ወጪ ግምት ያቀርባል። የሰሥራ ማስኬጃ ወጪ ግምት የሚሰላው በሚኒ/አነስተኛ ግሪድ መመሪያ መሰረት ይሆናል።

## 3.6 የካፒታል ዋጋ

በኢንቨስትመንት ላይ የሚታሰበው የትርፍ

- Any loss/gain should be treated in accordance with the Uniform System of Accounts, where any revenue/loss is allocated to income statement over a specified time period;

## 3.4 Depreciation

The regulated licensees are required to provide the following information on regulatory depreciation:

- The current depreciation amount stated in the tariff application;
- Accumulated depreciation schedule for the RAB for each asset class, and for each segment of the electricity sector;
- The current depreciation methodology must be determined based on the *Mini Grid Directive*.

## 3.5 Working Capital

The licensee must also provide estimate of working capital requirements, which are needed to sustain on-going operations. The working capital allowance has to be estimated in accordance with the formula in the *Mini Grid Directive.*

## 3.6 Cost of Capital

Since the return on investment is calculated as a product of WACC and RAB, the

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

ምጣኔ የሚሰላው በአማካይ የካፒታል ዋጋ (WACC) እና ቁጥጥር በሚደረግበት የንብረት (RAB) መሰረት እደመሆኑ፤ ባለፈቃዶች በባለስልጣኑ በኩል በሚኒ/አነስተኛ ግሪድ መመሪያ መሰረት በንጽጽር የሚወጣውን አማካይ የካፒታል ወጪ መጠንን ለኢንቨስትመንት ትርፍና ለተፈላጊ የገቢ መጠን ትመና መጠቀም አለባቸው፡፡

### 3.7 የስራማስኬጃ ወጪዎች

ስለ ስራማስኬጃ (ኦፐሬሽን)ወጪ መረጃ ሲያቀርቡ ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፤

- የሥራ ማስኬጃ ወጪ ሁሉንም የካፒታል ወጪ ማካተት የለበትም፡፡
- የስራ ማስኬጃ ወጪዎች መረጃ በሚከተሉት የኢንዱስትሪው ጠስራ ዘርፍ፤ የማመንጨት፣ የማከፋፈልና የሽያጭ መሰረት ተለይቶ የሚቀርብ ይሆናል፡፡
- የወጪ መረጃው የተለያዩ የወጪ መደቦችን በግልጽ የሚጠቁም መሆን አለበት፤
- ባለፈቃዶች ለእያንዳንዱ የሥራ ማስኬጃ ለወጪው ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ቁልፍ ጉዳዩችን በመጥቀስ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፤
- ባለፈቃዱ ስለ ሰራተኞች ወጪ መረጃ

regulated licensees must use the benchmark WACC determined by EEA in accordance with the Mini Grid Directive, to calculate the return on investment in the revenue requirements formula.

### 3.7 Operating Expenses

In submitting information on operating expenditure (opex), the license has to take account of the following:

- That the operating expenditure must exclude all capital expenditure (capex);
- Opex information are to be disaggregated according to the following segments of the electricity industry; Generation, and Distribution & Sale;
- The cost information must clearly indicate the different cost categories;
- Licensees must provide justification on key cost drivers for each opex category;
- The licensee must provide information

Off grid tariff application and information submission FINAL Procedure July 2021

ማቅረብ አለበት፣ ይህም በሚከተሉት መሰረት ተዘርዝሮ መቅረብ አለበት፤

i. ደመወዝ፤

ii. የትርፍ ሰዓት ክፍያ፤

iii. የህክምና ወጪዎች ወዘተ

- ማንኛውም በዝርዝር ማስረጃ የተደገፉ የሠራተኞች ደመወዝ ጭማሪ በመቶኛ ወይንም ሌላ ወጪ ከነማስረጃው ለባለስልጣኑ ለግምገማ መቅረብ አለበት፡፡

### 3.8 የጥገና ወጪዎች

ከስራ ማስኬጃ ወጪ በተጨማሪ ባለፈቃዱ ከታች የተዘረዘሩትን በሞሸፍን መልኩ ሁሉንም የጥገና ወጪዎችን የሚመለከት መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

ሀ. ቁሳቁሶች፣

ለ. የጉልበት ሥራ ወጪ፣

ሐ. ሌሎች ወጪዎች፣

- ባለፍቃዶች በታሪፍ ትግበራ ጊዜ ውስጥ ያለውን ማንኛውም የጥገናና የእድሳት ወጪ መጨመር ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤
- የጥገና ወጪ የንብረቶችን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያሳድጉበት ሁኔታ ልዩልዩ አካላቱን አሻሽሎ ለመቀየር የወጣ ወጪን ሊያካትት አይገባም፡፡ የላቀ የቁጥጥር አሰራር እንደሚያመላክተው

on staff expense and this should be broken down to reflect the following, among others:

i. Salaries;

ii. Overtime;

iii. Medical expenses etc.

- Any proposed percentage increase to staff salary or other staff expense must be supported with detailed justification to EEA for the forecast period for review.

### 3.8 Maintenance Expenses

In addition to the opex, the regulated licensees has to submit information on all repairs and maintenance expenses to cover the following items:

a. Materials;

b. Labour;

c. Other expenses:

- Licensees has to provide justification for any increase in repairs and maintenance expenses over the tariff period;
- Maintenance expense must exclude **asset retrofits and refurbishments** which enhance the **economic useful lives of assets**. In line with best regulatory practice, such expenses would be

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

እንዲህ አይነት ወጪዎች ወደ ቁጥጥር የሚደረግበት መነሻ ንብረት (on Regulatory Asset Base (RAB) ይጨመራሉ (capitalized)፡፡

### 3.9 የባለዕዳ መረጃ

የታሪፍ ማመልከቻ ከታች በተዘረዘረው አንጻር ስለተበዳሪዎች ዝርዝር ማቅረብ አለበት፤

- በየደንበኞቹ ዓይነት ያላለቀ ዕዳ ካለ፣
- በማይመለስ ብድር ስም የተለየ ብድር ከነማስረጃው፤
- የዕዳዎች ዕድሜ ትንተና፣
- የተሰረዘ እዳ ካል፣
- ዕዳዎችን ጨምሮ ማንኛውንም ተያያዥ ወጪ ለመመለስ የታቀደ እቅድ፡፡

### 3.10 የጋራ ወጪ ከተፈፀመ

የአንዳንዶቹ የአገልግሎት ኩባንያዎች ወጪዎች ከማእከል የሚጋሩና ከየትኛውም የተለየ የአሌሌክትሪክ ኢንዱስትሪ ክፍል ጋር በቀጥታ የተያያዙ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህም ሊከሰት የሚችለው ሁሉንም የኤሌክትሪክ ንግድ ስራ ማለትም የማመንጨት፤ የማስተላለፍ፤ የማከፋፈልና የመሸጥ ስራ አንድ አካል ጠቅልሎ ሲያስተዳድር ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ዝርዝር ጉዳዮች ማቅረብ ይጠበቅበታል

capitalized and added to the RAB;

### 3.9 Debtor Information

The tariff applicant must supply the following details on debtors:

- Outstanding debt per customer category, if any;
- Any provisions made for bad debts and justification for that;
- Age analysis for the debts;
- Debt write-off, if any;
- Plans to recover debts plus any associated costs;

### 3.10 Shared Cost if applicable

It is possible that some of ***the utility company costs are centrally shared*** and may not be directly linked to any particular segment of the electricity industry. This is likely to be the case if one entity operate in more than one segment of the electricity industry (i.e. generation and or generation, and distribution). In such an event, the licensee would be required to provide the following details:

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

- ማንኛዉም ማእከላዊ በሆነ መንገድ የሚተዳደር ወጪ በግልጽ መታወቅና መለየት አለበት፣
- በክፍሎች መካከል ያለውን ወጪ መጋራት መሰረት በግልጽ መለየትና መዘርዘር አለበት። ይህም ከላቀ ቁጥጥር ከሚደረግበት ወቺ አመዳደብ ዘዮ አንጻር በባለስልጣኑ የሚገመገም
- ወጪው ቁጥጥር በሚደረግበት ቁጥጥር በማይደረግበት ንግድ ሥራ መካከል ል የሚካፈል ከሆነ የክፍፍሉ መነሻ በመቶኛ ወይም የወጪ አመዳደቡ ለባለስልጣኑ ለግምገማ መቅረብ አለበት፣

## 3.11 የፍጆታ ና የሽያጭ ገቢ ትንበያዎች

የሽያጭ ገቢ ትንበያን በተመለከተ ቁጥጥር በሚደረግበት ባለፈቃድ ሊቀርብ የሚገባው አነስተኛ የመረጃ መስፈርት የሚከተለው ነው።

### 3.11.1 የሽያጭ ገቢ

- በእያንዳንዱ ደንበኛ መደብ ሊሰበሰብ የታቀደ የሽያጭ ገቢ፣
- ከውጭ ንግድ የሚገኝ ገቢ፣
- ለእያንዳንዱ ደንበኛ መደብ የኢነርጂ ሽያጭ መጠን ኪሎዋሰዓት (kWh)
- ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት

- Any centrally administered cost must be clearly defined and identified;
- Basis for cost sharing between the segments must be explicitly spelt out. This would be reviewed by EEA, based on best practice regulatory cost allocation methodologies;
- If the costs are shared between the regulated and the non-regulated business, the basis of the percentage split or cost allocation must be provided, for review by EEA;

## 3.11 Projected Sales Revenue and Demand Forecasts

Regarding the sales revenue forecast, the minimum information requirements to be provided by the regulated licensee are as follows:

### 3.11.1 Sales Revenue

- Sales revenue per customer class *where applicable*;
- Net export revenues;
- Energy sales volume (kWh) for each customer category;
- Projected total energy sales for

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

የኢነርጂ ሽያጭ ትንበያ፣

### 3.11.2 የኢነርጂ እና የኃይል ፍላጎት ትንበያ

- ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት በእያንዳንዱ ደንበኛ መደብ የኢነርጂ (kWh) ኪሎዋት በሰዓት ፍላጎት ትንበያ፣
- ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት ከፍተኛ የኃይል ኪሎዋት፣ (kW) ፍላጎት ተንበያ፤

### 3.11.3 የኢነርጂ ማስተላለፊያ/ማከፋፈያ አገልግሎት

- የተስተላለፈ ኢነርጂ (እንደ አግባቡ)
- ለተተነበየው ፍጆታ የሚሆን አቅርቦትን በማተላለፍ/በማከፋፈል ስራ መስመር ላይ ያለ የብክነት መጠን።

## 4. የገቢና ወጪ ዝርዝር እና የገቢ መግለጫ መረጃ

### 4.1 የማመንጫ ዘርፍ

ለማመንጫ ባለፈቃድ የታሪፍ ማመልከቻ ሲቀርብ ከገቢና ወጪ ዝርዝር እና የገቢ መግለጫ ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን መረጃዎች ያካተተ ይሆናል። ሁሉም የመለኪያ መስፈርቶችን እንደ ኪሎዋት ኪሎ ዋት፤ ሰዓት፤ ኪሎ ቮልት አምቲየር፣ ብር

the **next four years;**

### 3.11.2 Energy and Demand Projections

- Projected energy demand (kWh) per customer class, where applicable, for next four years;
- System Peak demand projections (kW) for the **next four years;**

### 3.11.3 Energy Wheeling

- Energy wheeled, if applicable;
- Line losses ( Distribution) arising from wheeling to meet expected demand.

## 4. Balance Sheet and Income Statement Information

### 4.1 Generation Sector

For generation licensees, submission of tariff application shall include the following information related to the Balance Sheet and Income Statement. All amounts shown must include units of measure such as: KWh, KVA, KW, Birr and Birr/KWh. Cost information must be provided in clear and

Official tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

እና ብር በኪሎዋት ሰዓት ማካተት አለባቸዉ፡፡ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ዝርዝርና ጥልቀት ያለው ትንታኔ ተዛማጅ በሆኑ ወጪዎች ላይ ለመስራት እድዲያስችለው የወጪ መረጃ በግልጽ እና በማያሻማ መልክ ሊቀረብ ይገባል፡፡

ሊሰጥ የሚገባው ዝርዝር መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል

- ለቀደሙት ሁለት ዓመታት (እንደ አግባቡ) ኦዲት የተደረገ የገቢና ወጪ ዝርዝር እና ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት የታሪፍ ዓመቱን ያካተተና የተተነበየ የገቢና ወጪ ዝርዝር፣

- የገቢና ወጪ ዝርዝር መረጃ (በአሁኑ ጊዜ ያለዉም ሆነ የሚገመተዉ) የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል
    - ጠቅላላ የንብረት ዋጋ፣
    - አጠቃላይ የአገልግሎት ተቀኛሽ፤
    - የቋሚ ንብረት ዋጋ፣
    - በእጅ ላይ የሚገኙ ንብረቶች ዝርዝር፤ (ኢንቬንቶሪስ)
    - የተፋይ ሒሳቦች፣
    - የተሰብሳቢ ሒሳቦች፣
    - የአጭር ጊዜ ዕዳ፣
    - ሌሎች ወቅታዊ ዕዳዎች፣
    - የረጅም ጊዜ ዕዳ፣

unambiguous manner, to enable the regulator perform detailed and in-depth analysis of all relevant cost components. The detailed information to be provided are as follows:

- **Audited Balance Sheet** for the previous **2 years** (*where relevant*) and forecasted balance sheet for the **next 4 years,** including the tariff year;

- The data for the **Balance Sheet** (actual or estimate) should include the following:
    - Gross Asset Value;
    - Accumulated depreciation;
    - Fixed Asset Value;
    - Inventories breakdown;
    - Accounts Payable;
    - Accounts Receivable;
    - Short-term Debt;
    - Other Current Liabilities;
    - Long-term Debt;

Off grid tariff application and information submission FINAL Procedure July 2021

- ➢ ከጠቅላላ ብረት ላይ እዳዎች ተቀንሰው የሚቀርየተጣራ ሀብት የተጣራ ሃብት (ኢኩቲ)፡፡

- የታሪፍ ዓመቱን ጨምሮ ለቀደሙት ሁለት የፋይናንስ ዓመታት ( እንደአግባቡ) ኦዲት የተደረገ የገቢ መግለጫ እና ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት(የታሪፍ ስሌት አመቱን ጨምሮ) የተነበየ የገቢ መግለጫ፡፡ የገቢ መግለጫ ትንቤያው ሲሰራ የኢነርጂ ሽጭ በኪሎዋት ሰአት በወቅቱ ባለው ታሪፍ ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፣

- ለገቢ መግለጫዉ (ወቅታዊውንና ትንበያውን) ደጋፊ መረጃዎች የሚከተሉትን ማካተት ይኖርባቸዋል፡-

  - ➢ የኤሌክትሪክሲቲ ሽያጭ
  - ➢ የነዳጅ ዋጋ (ብዛት እና በነዳጅ ዓይነት የሊትር ዋጋ እንደአግባቡ)፤
  - ➢ የሠራተኛ ወይም የሠራተኞች ወጪ፤
  - ➢ ዓመታዊ የአገልግሎት ተቀናሽ
  - ➢ የስራማስኬጃና የጥገና ወጪ በየዘርፉ፤
  - ➢ የአጭር ጊዜ ወጪ፤
  - ➢ የዕዳ ክፍያ ፕሮግራም፤
  - ➢ የግብር ወጪ አንደአግባቡ፤

- ➢ Equity;

- **Audited Income Statement** for the previous **2 financial years** (*where relevant*) and forecasted income statement for the following **4 years**, including the tariff year. The revenue for the forecasted income statement should be based on estimated sales (KWh) at current tariffs.

- **Supporting data** for the Income Statement (i.e. actual and forecasted) should include the following:

  - ➢ Electricity Sales;
  - ➢ Fuel cost (quantities and unit cost by fuel type(*where relevant*));
  - ➢ Employee or Staff Costs;
  - ➢ Annual depreciation;
  - ➢ Operating and maintenance expense breakdown;
  - ➢ Short-term expense;
  - ➢ Debt service schedule;
  - ➢ Tax expense, if any;

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

- ➢ የፍጆታ አስተዳደር DSM ወጪ እንደአግባቡ፣

- **የቴክኒክእና የንግድ መረጃ/ መለኪያዎች**

  - ➢ ወርሃዊ የኃይል ሽያጭና ተያያዥገቢና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚመጣ ገቢ፤
  - ➢ የለፈ ዓመት ዓመታዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ምርት እና ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት ትነበያ፤
  - ➢ ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት ዓመታዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ግዥ ትንበያ (እንደአግባቡ)፤
  - ➢ ወርሃዊ የከፍተኛ ሓይል (ኪሎዋት)ፍላጎት መጠን ስርዐት
  - ➢ በቀጣዮቹ አራት ዓመታት የከፍተኛ ፍላጎት ትንበያ፤

የማመንጫ ባለፈቃዱ የተለያዩ የኃይል ማመንጫዎችን በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ማቅረብ አለበት::

### 4.1.1 በነዳጅ የሚሰሩ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች

- በነዳጅ ዋጋ ላይ የተደረጉ የወጪ ግምቶች፤
- የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ግምት በዝርዝር ከታሳቢዎች ጋር፣
- ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት

- ➢ DSM expense, if any;

- **Technical and Commercial Data/Parameters:**

  - ➢ Monthly Energy sales and associated revenue;
  - ➢ Annual electricity production for previous year and projected for next four years;
  - ➢ Annual electricity purchases projected for next four years(*where relevant*);
  - ➢ Monthly system maximum peak demand (KW) ;
  - ➢ Projected system maximum peak demand for next four years.

The generation licensee has to submit detailed information on the various primary energy generation sources.

### 4.1.1 Thermal Power Plants

- Cost assumptions made on the fuel;
- Breakdown of operating cost and assumptions made;
- Energy output projected for next

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

የታቀደ የኢነርጂ ምርት፤

- የነዳጅ ሃይል ማመንጫዎችን አጠቃቀም እቅድ፤
- ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት የታሰበው የአቅም አጠቃቀመወ ምጣኔ (‰ ኪሎዋት) መጠን፤

**4.1.2 በውሃ ኃይል የሚሰሩ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎች**

የማመንጫ ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ያቀርባል

- ለእያንዳንዱ የሀይል ማመንጫ የምርት እቅድ፣
- የስራ ማስኬጃ ወጪ ዝርዝር፣
- አማካይ ዋጋ በተሸጠ ኢነርጂ (ኪሎዋት

**4.1.3 ታዳሽ የኃይል ማመንጫዎች**

- የስራ ማስኬጃ ወጪዎቻቸው ዝርዝርና ታሳቢዎች፤
- ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት የታሰበው የአቅም መጠን፣
- አማካይ ዋጋ በተሸጠ ኪሎዋት ሰአት፣

**4.1.4 ከግል ኃይል አምራቾች ተደረገ ግዢ**

የማመንጫ ባለፈቃዶች ከግል

four years;

- Thermal plant utilization plan;
- Projected capacity factor for next four years;

**4.1.2 Hydroelectric Power Plants**

The following shall be provided by the generation licensee:

- Production plans for each plant;
- Breakdown of operating cost;
- Average unit cost per KWh for sale;

**4.1.3 Renewable Energy Plants**

- Breakdown of operating cost and assumptions made;
- Projected capacity factor for next four years;
- Average unit cost per KWh for sale;

**4.1.4 Purchases from Independent Power Producers**

Generation licensees shall also

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

አምራቾች ስለተፈፀሙ ግዢዎች መረጃ ያቀርባሉ። መረጃው የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

- በየዓመቱ ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት በታሪፍ ጊዜ ከግል አምራቾች የሚገዙ መጠን በኪሎዋትሰዓት፣
- ከእያንዳንዱ ከግል አምራች የኃይል ግዢ ዋጋ፣
- ቀደም ሲል ካልቀረበ የተፈረመና በስራ ላይ ያለ የሃይል ግዢ ስምምነት ለባለስልጣኑ መቅረብ አለበት፣
- በስራ ላይ ባለዉ የሃል ግዢ ስምምነት ላይ የተደገረገ የፁሁፍ ማሻሻያ አንደአግባቡ፡

submit information on all purchases from IPPs. The information must include the following:

- Volumes (MWh) to be purchased from IPPs each year over the tariff period and for next four years;
- Cost of power purchase from each IPP;
- Submission of signed PPA of existing contracts to EEA, if not already submitted;
- Addendum or amendments to the existing PPA, if any;

## 4.2 የማከፋፈያ እና የሽያጭ ፈቃድ

ይህ ክፍል የታሪፍ ክለሳ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ የማከፋያ ባለፈቃዶች ማቅረብ ባለባቸዉ የመረጃ ዓይነት ላይ ያተኩራል። ባለፍቃዶች ሁሉም አባሪ ማስረጃዎች ና ሰነዶች በወረቀትና በኤሌክተሮኑክስ ቅጂ መቅረብ ያለባቸው መሆኑን ያስተወሏል። የሚከተሉት መረጃዎችና በታሪፍ ማመልከቻው ውስጥ ሊካተቱ ይገባል፣ እና ሁሉም የመስፈሪያ አሃዶች እንደ KWh፣ KVA፣ KW፣ Birr፣ Birr/KWh፣ ወዘተ ያሉትን ያካትታሉ።

## 4.2 Distribution & Sales Licensees

This section focuses on the type of data which the ***network licensees*** must submit when requesting for a tariff review. Licensees are to note that all schedules are to be submitted in both hard copy and electronic form. The following data and information are to be included in the tariff application, and all amounts shown should include the units of measure such as: KWh, KVA, KW, Birr, Birr/KWh, etc.

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

- ላለፉት ሁለት ዓመታት (አንደአግባቡ) አሁን በስራ ላይ ያለና ኦዲት የተደረገ የገቢና ወጪ ዝርዝር፣
- ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት የገቢና ወጪ ዝርዝር ትንበያ፣
- የገቢና ወጪ ዝርዝር ደጋፊ መረጃ የሚከተሉትን ነገሮች መሸፈን ይኖርበታል፡፡
  - ➢ ጠቅላላ የንብረት ዋጋ፣
  - ➢ የተጠራቀመ የአገልግሎት ተቀናሽ፤
  - ➢ ግንባታ ከላይ ያለ የቋሚ ንብረትና የማጠናቀቂያ ግዜው፤ ነት
  - ➢ ቀሪ ንብረቶች (ኢንቬንቶሪ)፤
  - ➢ ተከፋይ ሒሳቦች፣
  - ➢ በየደንበኞች መደብ ተሰብሳቢ ሒሳቦች፣
  - ➢ የአጭር ጊዜ ዕዳ፣
  - ➢ ሌሎች ወቅታዊ ዕዳዎች፣
  - ➢ የረጅም ጊዜ ዕዳ፣
  - ➢ ከዕዳ የተጣራ ጠቅላላ ንብረት ንብረት (ኢኩቲ)
- ላለፉት ሁለት ዓመታት (እንደአግባቡ) አሁን በስራ ላይ ያለና ኦዲት የተደረገ የገቢ መግለጫ፣
- ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት የገቢ ትንበያ፡፡ የገቢ ትንበያው በተገመተ

- Actual and audited Balance Sheet for the **previous 2 years**(*where relevant*)**;**
- Projected Balance sheet for the **next four years;**
- Supporting data for the Balance sheet should cover the following items:
  - ➢ Gross asset value;
  - ➢ Accumulated depreciation;
  - ➢ Fixed Asset Works-In-Progress and scheduled completion dates;
  - ➢ Inventories;
  - ➢ Accounts payable;
  - ➢ Accounts receivable by customer category;
  - ➢ Short-term debt;
  - ➢ Other Current liabilities;
  - ➢ Long-term debt;
  - ➢ Equity
- Actual and audited Income Statement for the previous **2 years**(*where relevant*)**;**
- Projected income statement for the next **4 years.** Projected revenue should be based

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

ሽያጭና በወቅታዊ ታሪፍ ላይ የተመሰረተ ሽያጭ ላይ መሆን አለበት፣

- የገቢውን መግለጫ የሚደግፉ መረጃዎች የሚከተሉትን ጉዳዮች ማካተት ይኖርባቸዋል
  - ➢ የኤሌክትሪክ ሽያጭ ለእያንዳንዱ ደንበኛ መደብ ( የሽያጩ መጠንና ተጕዳኝ ታሪፍን)፣
  - ➢ የጅምላ አቅርቦት ዋጋ (የማመንጫ ዋጋና በተጨማሪም የግዢ ታሪፍ)፣
  - ➢ የተቀጣሪ ወይም የሰራተኞች ወጪ፣
  - ➢ ዓመታዊ የአገልግሎት ተቀናሽ፤
  - ➢ የስራ ማስኬጃና የጥገና ወጪ ዘዝርዝር፣
  - ➢ የፍጆታ አስተዳደር (DSM) ወጪ እንደአግባቡ፤
  - ➢ የአጭር ጊዜ ወለድ ወጪ፣
  - ➢ የረጅም ጊዜ ወለድ ወጪ የዕዳ ክፍያ ፕሮግራምን ያካተተ(እንደአግባቡ)፣
  - ➢ የግብር ክፍያ (እንደአግባቡ)፣
- ከእያንዳንዱ ደንበኛ መደብ አንጻር የገቢ መስፈርት መጠን፣
- ለእያንዳንዱ ደንበኛ መደብ የቀረቡ የታሪፍ ተመን፣
- የሚከተሉትን የሚያሳዩ የቴክኒክና የንግድ መረጃ/ መለኪያዎች፣
  - ➢ የኢነርጂ ግዥዎች፤

on estimated sales at current tariffs;

- Supporting data for the Income Statement should cover the following items:
  - ➢ Electricity sales per customer class (i.e. quantities and associated tariffs);
  - ➢ Bulk Supply Costs (Generation plus tariffs);
  - ➢ Staff or Employee Cost;
  - ➢ Annual Depreciation;
  - ➢ Operating and Maintenance Expense Breakdown;
  - ➢ DSM Expense, if any;
  - ➢ Short term interest expense;
  - ➢ Long-term interest expense, include debt service schedule if any;
  - ➢ Tax expense, if any;
- Proposed Revenue Requirements per end-use customer class:
- Proposed tariffs for each customer category;
- Technical and Commercial Data/Parameters showing the following:
  - ➢ Energy purchases;

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

- የኢነርጂ ሽያጭ.
- ቴክኒካዊና ቴክኒካል ያልሆነ ብክነት (እንደ አግባቡ)፣
- በእያንዳንዱ የቮልቴጅ መጠን የኃይል ብክነት (እንደ አግባቡ)፣
- በእያንዳንዱ የደንበኛ መደብ የኃይል የኢነርጂ ሽያጭ እና ገቢ፣
- የደንበኞች ብዛት ቤታሪፍ መደቡ፣
- ለአሁኑ ዓመት ወርሃዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ግዢ (እንደ አግባቡ)፣
- ባለፉት አመታት የተመዘገበ ከፍተኛ የወርሃዊ የኃይል ፍላጎት (እንደ አግባቡ)፣
- ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት በየዓመቱ የኤሌክትሪክ ኃይል ገዢ ትንበያ (እንደ አግባቡ)፣
- ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት ለሽያጭ የታሰበዉ የኤሌክትሪክ ኃይል ትንበያ፣
- ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት የታሰበ የከፍተኛ የኃይል ፍላጎት ትንበያ፣

- ለሁሉም የደንበኛ ክፍሎች የቀረቡ ታሪፍ ጥያቄ፤

ሀ. የቤተሰብ/የመኖሪያ ቤት፣

ለ. ጠቅላላ/ የንግድ (እንደ አግባቡ)፣

ሐ. ኢንዱስትሪ (እንደ አግባቡ)፡፡

በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የተሰጠ ማብራሪያ

- Energy sales;
- Losses: Technical and Non-technical, if applicable;
- Energy losses per voltage level, if applicable;
- Energy sales and revenue per customer class;
- Number of customers per tariff category;
- Monthly electricity purchases for current year(*where relevant*);
- Monthly system maximum demand recorded for previous years (*where relevant*);
- Projected annual electricity purchase for next four years(where relevant);
- Projected annual electricity sales for next four years;
- Projected system maximum demand for next four years

- Proposed Tariffs for all the end-user classes:

a. Domestic/Residential

b. General /Commercial, *as applicable*

*c.* Industrial: *as applicable*

Explanation provided on the following issues *as*

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

(እንደ አግባቡ)፣

- ውጤታማነትን ለማሻሻል የተደረገ ጥረት፣
- የቴክኒክ ብክነት መጠንን የመቀነስ ዕቅዶች፣
- ቴክኒካል ያልሆነ ብክነት የመቀነስ ዕቅዶች፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦችን ቆይታ ጊዜ የመቀነስ ዕቅዶች፣
- የአገልግሎት ጥራትን የማጎልበት እና የሀይል መቆራረጥ የቆይታ ጊዜንና ድግግሞሽን ለመቀነስ የተደረጉ ጥረቶች (ማለትም የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት)፣

**4.3 የፍጆታ አስተዳደር DSM እንደአግባቡ ለሚኒ ግሪድ አቅርቦት**

ባለስልጣኑ የታሪፍ ግምገማ በሚያከናውንበት ጊዜ ተጠቃሚዎች የኃይል ብቃትና ቁጠባ ልምምዶችን እንዲከተሉ ለማበረታታት ባለፈቃዶች የሚያደርጉትን ጥረት ግምት ውስጥ ያስገባል:: በዚህ ረገድ፣ የተፈቀደውን የፍጆታ አስተዳደር ወጪዎች (DSM costs ) የባለፈቃዱ የገቢ መስፈርት አካል ተደርገዉ ሊቆጠሩ ይችላሉ:: የፍጆታ አስተዳደር ወጪዎችን በተመለከተ በመረጃ የተደገፈ ዉሳኔ ለማድረግ ባለስልጣኑ ባለፈቃዶች የሚከተሉትን መረጃዎች እንዲያቀርቡ

*applicable* :

- efforts to improve efficiencies;
- plans to reduce technical loss level;
- plans to reduce non-technical losses;
- plans to reduce accounts receivable period;
- efforts to enhance quality of service and reduce duration and number of outages **(i.e. quality of service delivery);**

**4.3 Demand Side Management as applicable for the mini grid system**

In carrying out the tariff review, EEA will take account of efforts by the licensees to encourage consumers to adopt energy efficiency and conservation practices. In that regard, approved DSM costs could be considered by EEA as part of licensee's revenue requirements. In order to make informed decision on DSM costs, EEA would require the licensees to provide the following information:

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

ይጠይቃል፡፡

የፍጆታ አስተዳደር ስትራቴጂ፡- የታሪፍ ጊዜን የሚሸፍኑ ዕቅዶችና መርሀግብሮች፣

- በታሪፍ ጊዜ ውስጥ የቀረበው የፍጆታ አስተዳደር በጀት፣
- ዝርዝር የፍጆታ አስተዳደር በሁሉም ወጪ ዓይነቶች አንር የተለየ
- ለፍጆታ አስተዳደር ወጪዎች የፕሮገራሙን ውጤት ጨምሮ ማብራሪያባና ማስረጃ፤

DSM strategy, plans and programs covering the tariff period;

- Proposed DSM budget over the tariff period;
- Breakdown of DSM costs, with all cost items clearly identified;
- Explanation and justification for the DSM expenses, including expected benefits of the programs;

## 5. የገቢ መስፈርቶች መረጃ

ባለፈቃዶች በሚኒ ግሪድ መመሪያ መሠረት በአጠቃላይ የገቢ መስፈርቶች ላይ ሁሉንም መረጃዎች እና ስሌት ማጠቃለያ እንዲያቀርቡ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በቀረበው ታሪፍ እንዲሰበሰብ የሚፈለገው የገቢ መጠን በየደንበኞች መደብ ተለይቶ መቅረብ አለበት፡፡

የጠቅላላ ገቢ መስፈርት ማጠቃለያ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡፡

ሀ. ቁጥጥር የሚደረግበት ንብረት መነሻ RAB

ለ. የኢንቨስትመንት ተመላሽን ለማስላት ጥቅም ላይ የዋለዉ አማካይ የካፒታል ዋጋ WACC ቁጥጥር በሚደረግበት ንብረት (RAB)፤

ሐ. በሚኒ ግሪድ መመሪያ ውስጥ እንደተገለጸው

## 5. Revenue Requirements Information

The licensees are required to provide a summary of all the information and calculation on the total revenue requirements, in accordance with the *Mini Grid Directive.* The total revenue to be recovered from the proposed tariff should be disaggregated according to each customer class.

The total revenue requirement summary must include the following:

a. RAB;

b. The WACC which was used as rate of return and applied to RAB, to calculate the return on investment;

c. Total Revenue Requirements showing the

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021

የተለያዩ የወጪ ክፍሎችን የሚያሳዩ የጠቅላላ የገቢ መስፈርቶች

## 5.1 የታሪፍ አወቃቀር መረጃ

### 5.1.1 የማከፋፈያ እና የሽያጭ ታሪፍ

የማከፋፈያ ባለፈቃዱ ለሽያጭ ኃላፊነት ያለበት እንደመሆኑ፤ ባለፈቃዱ ከታሪፍ ማመልከቻው ጋር የሚከተሉትን መረጃዎች መስጠት አለበት፡፡

- በየታሪፍ/ደንበኛ መደብ ፤ የሽያጭ መጠንን፤ የታሪፍ ጭማሬንና፤ ከታሪፍ የመገኘ ጊ ታሳቢዎችን፤
- የታቀደው የታሪፍ አወቃቀር ዝርዝርና የቀረበው የታሪፍ መዋቅር በደንበኞች ላይ ሊያሳድር የሚችለው የሚያሳድረው ተጽዕኖ፣

## 5.2 ታሪፍ

ባለፈቃዱ የሚከተሉትን መረጃዎች እንዲያቀርብ ይጠየቃል፤ በባለፍቃዱ የተቀመጡ ታሳቢዎች፤

- የታቀደ ታሪፍ ፣ (የሲስተም አስተዳደር ወጪን ጨምሮ
- የድጋፍ አገልግሎቶች( Ancillary services) ክፍያዎችን

various cost components, as defined in the *Mini Grid Directive*;

## 5.1 Tariff Structure Information

### 5.1.1 Distribution and Sale Tariff

Since the distribution licensee is also responsible for sale, the licensee must provide the following information as part of its tariff application:

- Assumptions made for each customer or tariff category, including expected volume sales, tariff increase and expected revenues from retail tariffs;
- Details of proposed tariff structure and impact of proposed structure on consumers.

## 5.2 Tariff

The licensee is required to provide the following information: Assumptions made by licensee;

- Proposed tariff, including System Operator fee *as applicable*
- Ancillary services costs;

application and information submission FINAL procedure July 2021

## 5.3 የታሪፍ ማመልከቻ አባሪዎች ክፍል

ሁሉም ተያያዥነት ያላቸዉ ሰንጠረዦች እና መረጃዉን የያዙ ማጣቀሻዎች እንዲሁም ማንኛዉንም መረጃ በታሪፍ ማመልከቻዉ አባሪ ክፍል መካተት አለባቸዉ፡፡

## 5.3 Appendices Section of Tariff Application

All relevant tables and templates containing the data as well as any information, must be included in the appendices section of the tariff application.

Off grid tariff application and information submission FINAL procedure July 2021